በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ:245259

6/2/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡-ተመስገን ድንጋጎ እና ቤተሰቡ ሃ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ አቶ ክፍሌ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ሰናይት እሸቱ የአቶ እሸቱ ሰለሞን ወልደየስ ባለቤት እና የህጻን ናኦል ሰለሞን እና የማራናታ ሰለሞን አሳዳጊ ጠበቃ አቶ ፍቃዱ ይልማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦ/ጠ/ፍ/ቤት ምስራቅ ኦሮሚያ ቋሚ ችሎት ሆኖ አመልካች ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል።ተጠሪ በቀን 8/4/2010 ዓ ም አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ባለቤቴ ሰለሞን ወልደየስ መኪና ሲያሽከረክር በቀን 29/3/2013 ዓም በአመልካች መኪና ተገጭቶ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሞቱ እድሜው 32 ዓመት የነበረ በመሆኑ የወር ደሞዙ 20,000 (ሃያ ሺ) ስለነበር እስከ 60 ዓመት ስለሚኖር በህይወት ቢኖር ሊከፍለን ይችል የነበረው በዚሁ ተባዝቶ ለተጠሪና እና ለልጆቻቸው በፍ/ህ/ቁ፤2095 መሰረት ካሳ፤ በተጨማሪም የቀብር ማስፈጸሚያና ለ40 ስነ ስርዓት ዝግጅት ወጪዎች እንዲሁም የጠበቃ አበል ጭምር ተደምሮ አመልካች እንዲከፍል ተብሎ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በሰጠው መልስ የተጠሪ ባል ደምወዙ 20000(ሀያ ሺ) ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፤ 60 አመት ሊኖር ይችል እንደነበረም ማረጋገጫ የለም፤ካሳ ክፍያው ሊጠየቅ የሚገባውም በቀለብ መልክ ነው፤ተጠሪ ሰርቶ መብላት የማይችሉበት ምክንያት ካለ ብቻ ነው ለራሳቸው ቀለብ መጠየቅ የሚችሉት፡፡እንዲሁም ተሽከርካሪው የኢንሹራንሽ ሽፍን ያለው በመሆኑ ሉሲ ኢንሹራንስ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ፤43(1) መሰረት ጣልቃ እንዲገባ ጠይቆ፤ በአጠቃላይ ተጠሪ ያቀረቧቸው ወጪዎች እና የዋጋ ግምቶች የተጋነኑ መሆኑን በመግለጽ ተከራከረ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ የተጠሪ ባለቤት በአመልካች መኪና መገጨቱንና ጉዳት መድረሱን ተረጋግጦዋል በማለት ነገር ግን ተጠሪ ለራሳቸው የጠየቁትን ወጪ በተመለከተ ተጠሪ ሰርተው መብላት የማይችሉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነገር የሌለ በመሆኑ ውድቅ እንዲሆን ወሰነ፡፡

ለህጻናቱ አባታቸው በሂወት ቢኖር ለእያንዳንዳቸው በወር ብር 2,500 (ሁለት ሺ አምስት መቶ) ያወጣ እንደነበር በመያዝ እድሜያቸው 18 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ የሚከፈላቸው ብር እና የቀብር ወጪ በርትእ 70,000 (ሰባ ሺ ብር) በመውሰድ በጠቅላላ በድምሩ ብር 852,000 (ስምንት መቶ አምሳ ሁለት ሺ ብር) የጠበቃ አበል 15% እና ወጪ ኪሳራ የዳኘነት ተጨምሮ እንዲከፍሉ ሲወስን፤ ከዚህ ውስጥ የስር ጣልቃ ገብ ሉሲ ኢንሹራንስ ብር 40,000 (አርባ ሺ ብር) እንዲከፍል በማለት ወሰነ፡፡አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ፤337 መሰረት አጸናው፡፡

የሰበር ችሎቱም በቀረበለት አቤቱታ ላይ ተመስርቶ ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የሟች አቶ ሰለሞን ወልደየስ የወር ደሞዝ ብር 2500 (ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር) መሆኑን በመ ቁ፤32183 በቀን 14/4/2014 ዓም ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ አሁን በተያዘው ጉዳይ ለሟች ሁለት ልጆች በየወሩ ለያንዳንዳቸው ብር 2500 ( ሁለት ሺ አምስት መቶ) ይሰጥ ነበር ተብሎ የቀለብ ካሳ የመወሰኑን አግባብነት እንደ ጭብጥ በመያዝ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ በማስቀረብ አከራክሮዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ፤በዚህ መዝገብ ከተያዘው ጭብጥና እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል።አመልካች ያቀረበው የቅሬታ ነጥብ ከአንድ በላይ ቢሆንም፤ ውሳኔ የሰጠነው መዝገቡ ሲያስቀርብ በተያዘው ጭብጥ ላይ ብቻ ተመስርተን ነው።

በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ተጠሪ ከአሰሪ ለጠየቁት ካሳ አሰሪው የሟች ደሞዝ ብር 2500(ሁለት ሺ አምስት መቶ) ነበረ በማለት ባቀረበው ላይ በመመስረት በመ/ቁ32183 ተወስኖ ለተጠሪ ካሳ ብር 155000(አንድ መቶ አምሳአምስት ሺ) የተወሰነ ስለመሆኑ ከክርክሩ ተረድተናል።ይህ እንዳለ ሆኖ ተጠሪ በዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር የሀረርጌ ህዝብ ማመላለሻ አስጫኝ ማህበር ሟች ከጅጅጋ አዲስአበባ በወር ስምንት ግዜ እንደሚሄድና አንድ ግዜ ሲሄድ ብር 2500(ሁለት ሺ አምስት መቶ) እንደሚያገኝ፤ በወር ስምንት ግዜ ሲሄድም ብር 20000(ሀያ ሺ) ያገኝ እንደነበረ ማስረጃ ሰጥቶ ነው የተወሰነልኝ ብለው ተከራክረዋል። አመልካች ደግሞ በመልስ መልሱ ይህ ማስረጃ አልቀረበም አላለም። ስለዚህ የሟች ደሞዝ 2500(ሁለት ሺ አምስት መቶ) የነበረ ቢሆንም መኪና በመያዝ ወደጅጅጋ በሄደ ቁጥር ያገኝ ነበር ተብሎ ከተረጋገጠው የሟች ገቢ አንጻር ለሁለት ልጆቹ በየወሩ ለቀለብ ለያንዳንዳቸው ብር 2500(ሁለት ሺ አምስት መቶ) መክፈል የማይችል ሰው ነበር ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም። በመሆኑም የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለን ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሳኔ

- የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 370401 በታህሳስ 15/2015 የወሰነውና፤የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 240952 በመጋቢት 8/2015 ያጸናው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት አጽንተነዋል።
- በዚህ መዝገብ በሀምሌ 19/2015 የተሰጠውን እግድ አንስተናል። እግድ ለተላለፈላቸው ክፍሎች እግዱ መነሳቱ ይጻፍ።
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ።
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !